የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ–ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 52
ADDIS ABABA–29th April, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፪/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የመላ አፍሪካን ፓርላማ ለማቋቋም በአፍሪካ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ማቋቋሚያ ስምምነት ሥር ዩወጣውን ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፪ሺ፩፻፷፰

## CONTENTS

Proclamation No. 332/2003

Ratification of the Protocol to the Treaty Establishing the African Economic Community Relating to the Pan–African Parliament Proclamation .... Page 2168

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፪/፲፱፻፺፭
## የመላ አፍሪካን ፓርላማ ለማቋቋም በአፍሪካ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ማቋቋሚያ ስምምነት ሥር የወጣውን ፕሮቶኮል ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የአፍሪካ ኅብረት አካላት ውጤታማ ሆነው ማየት የሚፈለግ በመሆኑ፤

የመላ አፍረካ ፓርላማ መቋቋም የአፍረካ ሕዝቦችና እነሱን ከታች አንስቶ የሚወክሉ ችግሩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ድርጅቶች በአህጉሪቱ ተጋርጠውባት ባሉት ችግሮችና ፈታኝ ሁኔታዎች ውይይትና ውሣኔ አሰጣጥ ላይ የበለጠ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማስቻል የታሰበ የጋራ መድረክ በመሆኑ፤

የመላ አፍሪካ ፓርላማ የተቋቋመው የአፍሪካ ሕዝቦች በኢኮኖሚ ልማቱና የአፍሪካን አህጉር በማዋሃዱ ረገድ ሙሉ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማረጋገጥ በመሆኑ፤

የአፍሪካ ሕዝቦች በባህል፣ በርዕዮተ ዓለም፣ በዘር፣ በሃይማኖትና በብሔር ልዩነት የማይፈጠር አንድ ትልቅ ማኅበረሰብ ለመመስረት ላላቸው ታላቅ የኅብረት፣ የአንድነትና የጥምረት ምኞት ድጋፍ ማድረግ አስገዳጅና አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ በመሆኑ፤

ዲሞክራሲያዊ መርሆዎችንና ሕዝባዊ ተሳትፎን ማጠናከር፣ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትና ዲሞክራሲያዊ ባህልን ማዳበር እንዲሁም መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ የመላ አፍሪካን ፓርላማ ለማቋቋም በአፍሪካ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ማቋቋሚያ ስምምነት ሥር የወጣውን ፕሮቶኮል ለማፅደቅ የወሰነ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 332/2003
## A PROCLAMATION FOR THE RATIFICATION OF THE PROTOCOL TO THE TREATY ESTABLISHING THE AFRICAN ECONOMIC COMMUNITY RELATING TO THE PAN–AFRICAN PARLIAMENT

WHEREAS, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is desirous to see the effectiveness of the Organs of the African Union;

WHEREAS, the establishment of the Pan–African Parliamant is informed by a vision to provide a common platform for African Peoples and their grass-roots organizations to be more involved in discussions and decision-making on the problems and challenges facing the Continent;

WHEREAS, the Pan-African Parliament is established to ensure effectively the full participation of the African Peoples in the Economic Development and Integration of the African Continent;

WHEREAS, it is imperative and urgent to further consolidate the aspiration of the African Peoples for greater unity, solidarity and cohesion in a larger community transcending cultural, ideological, ethnic, religious and national differences;

WHEREAS, it is necessary to promote democratic principles and popular participation, to consolidate democratic inistitutions and culture to ensur good governance;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has accepted the Ratification of the Protocol to the Treaty Establishing the African Ecnomomic Community Relating to the Pan–African Parliament at its session held on 29th day of April, 2003;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የመላ አፍሪካን ፓርላማ ለማቋቋም በአፍሪካ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ማቋቋሚያ ስምምነት ሥር የወጣውን ፕሮቶኮል ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፪/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

"ማጽደቅ" እንደአስፈላጊነቱ ፕሮቶኮል ፀንቶ ከሆነ መቀበልን ይጨምራል።

፫· <u>ፕሮቶኮሉን ስለማፅደቅ</u>

የአፍሪካ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ማቋቋሚያ ስምምነት አባል አገራት በሆኑት በአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል አገራት እ·ኤ·አ· ማርች ፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ·ም በሰርት ሊቢያ የተፈረመው የመላ አፍሪካን ፓርላማ ለማቋቋም የወጣውን ፕሮቶኮል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዚህ አዋጅ አጽድቋል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም·

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት



NOW, THEREFORE, in accordance with sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ratification of the Protocol to the Treaty Establishing the African Economic Community Relating to the Pan-African Parliament Proclamation No. 332/2003."

2. Definition

"Ratification" includes Accession to the Protocol.

3. *Ratification of the Protocol*

The Protocol to the Treaty Establishing the African Economic Community Relating to the Pan–African Parliament adopted by the member states of the Organization of the African Unity states parties to the Treaty Establishing the African Economic Community, in Sirt, Libya, on 2nd March 2001, is hereby ratified by the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

4. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of 29th day of April, 2003.

Done at Addis Ababa, this 29th day of April, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE